# ዓለም አቀፍ ስምምነቶች እና ሦስተኛ መንግሥታት

ዶክተር ዝጂስዋብ ባትስዋብ ጋሊትስኪ*

ዓለም አቀፍ ስምምነቶች መንግሥታትን የሚያስገድዱ የሥነ ምግባር ሕግጋት በተስማሚዎቹ መንግሥታት ላይ ይመሠርታሉ ። ስምምነቶቹም ዓለም አቀፍ ፣ የተወሰነ ክፍለ ዓለምን የሚመለከቱ ወይም የተወሰኑ መንግሥታትን የሚመለከቱ ሊሆኑ ይችላሉ ። ተስማሚዎቹ መንግሥታትም በስምምነቶቹ የገቡባቸውን ግዴታዎች የሚጸረሩ ድርጊቶች መፈጸም የለባቸውም ፤

በፍትሐ ብሔር ታዋቂ በሆነው እና ከሮማውያን ፍትሐ ብሔር በተወሰደው "ፓክታ ተርቲስ ነክ ኖሰንት ነክ ፕሮሱንት" (ስምምነቶች ተፈጻሚነት የሚኖራቸው በተስማሚዎቹ ወገኖች ብቻ ነው) በሚለው መርህ (ማክሲም) መሠረት ስምምነቶች በሦስተኛ ወገኖች ላይ መብትም ሆነ ግዴታ ሊያስከትሉ አይችሉም ። ይህ መርህ በፍትሐ ብሔር የውል ሕግ ጠቅላላ አስተሳሰብ ላይ የተመሠረተ ሲሆን[1] በዓለም አቀፍ ሕግ ደግሞ በአገሮች ነፃነት እና የበላይ ገዥነት (ሶቨሬይኒቲ) ሕግጋት አንፃር ሲታይ ተጨማሪ ድጋፍ አለው ። ስለሆነም ፥ ዓለም አቀፍ ስምምነቶች ተፈጻሚነት ሊኖራቸው የሚገባው በተዋዋይ ወገኖች መካከል ብቻ ስለሆነ ፣ በመሠረቱ በስምምነቶቹ ተካፋይ ባልሆኑ ሦስተኛ አገሮች ላይ መብትም ሆነ ግዴታ አይመሠርቱም ።

ይህ መሠረተ ሐሳብ ተቀባይነት አግኝቶ የሚሠራበት ለመሆኑ ከስስምነት ለሚመነጭ ግዴታ መሠረቱ ፈቃድ ነው[2] በሚል መርህ ከተመሠረቱ የመንግሥታት አድራጎቶች ፣ የዓለም አቀፍ ፍርድ ቤቶች ውሳኔዎች እና የሕግ ምሁራን ጽሑፎች በቂ ማስረጃ ይገኛል[3*] ። የዚህንም መሠረተ ሐሳብ ተግባራዊ መሆን በሦስተኛ አገሮች ላይ ሊፈጸሙ ከማይችሉ መብቶችና ግዴታዎች ማየት ይቻላል ።

ለምሳሌ ፣ "በፖሊሽ አፐር ሳይለስያ ላይ ጀርመኔ ኣለኝ ስላለው መብት" ቋሚው የዓለም አቀፍ ፍርድ ቤት ከመጀመሪያው የዓለም ጦርነት በኋላ ጦርነቱን ለማቆም የተደረጉትን ልዩ ልዩ ስምምነቶች በማስመልከት እንደሚከተለው ወስኖአል ፦

"ስምምነት ተፈጻሚ የሚሆነው በተስማሚዎቹ አገሮች ላይ እንጂ በሦስተኛ አገሮች ላይ በቀጥታ ተፈጻሚ ነው ማለት እንደማይቻል ሁሉ ጦርነትን የማቆም ስምምነት ጠባይ ያለው ሰነድ ለሦስተኛ አገሮች በማንኛውም ሁኔታ ሁሉ መብት ይሰጣል ብሎ መገመት ፈጽሞ አይቻልም ። ስምምነት ሕግ የሚመሠርተው በተስማሚዎቹ መካከል ብቻ ነው ።"[4] በዚህ መሠረት ፍርድ ቤቱ ፖላንድ በጦርነቱ ማቆም ስምምነት ተካፋይ ስላልነበረች በስምምነቱ መጠቀም አትችልም በማለት ወስኗል ።

እንደዚሁም ፣ "የቾርሎው ፋብሪካ"ን በሚመለከት ጉዳይ ቋሚው ፍርድ ቤት ፖላንድ በጦርነት ማቆም ስምምነቱ ተካፋይ ስላልነበረች በስምምነቱ መጠቀም አትችልም በማለት ወስኗል ።[5]

በሦስተኛ አገሮች ላይ ወደፊት ግዴታን ይመሠርታሉ ተብለው የሚገመቱትን ዓለም አቀፍ ስምምነቶች በሚመለከት አንፃር "የኦደር ወንዝ ዓለም አቀፍ ኮሚሽን የወሰን ክልል" በሚመለከት ጉዳይ ቋሚው ፍርድ ቤት በብዙ አገሮች መካከል ተደርጎ የነበረው የባርሰሎና ስምምነት በስምምነቱ ተካፋይ ባልነበረችው በፖላንድ ላይ ተፈጻሚ ይሆናል ብሎ ለመወሰን አልፈለገም ። ፍርድ ቤቱ ፣ "የቨርሳይ ዓለም አቀፍ ስምምነት[6] እን

---

*ረዳት ፕሮፌሰር ሕግ ፋኩልቲ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ፣ በዓለም አቀፍ ሕግ ሌክቸረር ፣ ምርሶው ዩኒቨርስቲ ።

1 በሮም የውል ሕግ የታወቁትን "ግዴታ ሦስተኛ ወገንን አይመለከትም (አብሊጋስዮ ተርትዮ ኖን ኮንትራሂቱር) ፣ ስምምነቶች ከተስማሚዎቹ ውጭ በሌሎች ሰዎች ላይ ተፈጻሚ አይሆንም (ፓክታ ኖን አብሊጋንት ኒሰጀንተስ ኢንተር ኣሊኢኒሸያ) የሚሉትን መርሆዎች (ማክሲምስ) ይመለከቷል ።

2 "በዓለም አቀፍ ስምምነቱ ያልተካፈሉትን ብሔሮች (ሦስተኛ ብሔሮች ተብለው የሚጠሩ) ስምምነቱ ሊመለከታቸው የማይችል (ረስ ኢንተር አልየስ አክታ) በመሆኑ ስምምነቶች ከተስማሚዎች ውጭ በሦስተኛ ወገኖች ላይ ጥቅም ሆነ ግዴታ አያስከትሉም (ፓክታ ተርቲስ ነክ ኖሰንት ነክ ፕሮሱንት) የሚለው መሠረተ ሐሳብ በሕጋዊ አስተሳሰብ ሆነ በትክክለኛ አስተሳሰብ (ከሞን ሰንስ) የተደገፈ ነው ።" ሎርድ ማክነይር ፣ ዘሎው ኦፍ ትሪቲስ ፣ (ሎንደን ፥ እ ኤ አ ፲፱፻፷፭) ገጽ 309 ።

3 ቾ.ኤ.ሩሶ ፣ ፐሪንሲፐ ጀንር ዱ ድሮዋ ኢንተርናስዮናል ፑብሊክ ፣ (ፓሪስ እ ኤ አ ፲፱፻፵፱) በልዩም I ፣ ገጽ 453 ። በተጨማሪ የሚከተሉትን ይመለከቷል አር.ኤፍ.ሮክሰቡር ፣ ኢንተርናሽናል ኮንቨንሽንስ ኤንድ ተርድ ስቴትስ ፣ (በስቶን እ ኤ አ ፲፱፻፲፯) ገጽ 19 ፤ ኢ.ካቫል የሬ ፥ "ሪገል ጀነራል ዱ ድሮዋ ደ ላፐይ ፣ ረስወይ ደ ኩር ፣ አካዳሚክ ደ ድሮዋ ኢንተርናስዮናል ( ዘ ሒግ ፣ እ ኤ አ ፲፱፻፶፱) በልዩም 26 ፣ ገጽ 257 ፣ ዲ አምዚሎቲ ፣ ኩር ደ ድሮዋ ኢንተርናስዮናል ፣ (ጂ ጊደል ትርጉም ፣ ፓሪስ እ ኤ አ ፲፱፻፳፱) ፣ ገጽ 414 ፣ እና ኤል.ኤፍ.ኤል. ኦፐንሃይም ፣ ኢንተርናሽናል ሎው ኤ ትሪቲስ ፥ (፰ኛ እትም በኤች ላውተርፓኽት ፣ ሎንዶን ኒውዮርክ እ ኤ አ ፲፱፻፶፭) ፣ በልዩም ፩ ገጽ 995

ለአተረጓጐሙ ሲባል የጸሐፊው የግርጌ ማስታወሻ የትርጉሙ የግርጌ ማስታወሻ ፤ የጸሐፊው የግርጌ ማስታወሻ ፤ የትርጉሙ የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር ሆኖዋል ።

4 ፓብሊኬሽንስ ኦፍ ዘ ፐርማነንት ኮርት ኦፍ ኢንተርናሽናል ጀስቲስ ፣ ጀጅመንትስ ፣ኦርደርስ ኤንድ አድባይዘሪ ኦፒንዮንስ ፣ (እ ኤ አ ፲፱፻፳፮) ሲርይስ ኤ ቁ 7 ገጽ 24-29

5 ፒ.ሲ.አይ.ጄ. ፐርማነንት ኮርት ኦፍ ኢንተርናሽናል ጀስቲስ ማለትም ቋሚው ዓለም አቀፍ ፍርድ ቤት) ፓብሊኬሽንስ (እ ኤ አ ፲፱፻፳፰) ሲርይስ ኤ ቁ 17 ገጽ 43-46 ፣ አንዋል ዳይጀስት 1927-28 ጉዳይ ቁ. 286 ገጽ 416-17 ትንም ይመለከቷል ።

6 ይህ አንቀጽ ዓለም አቀፍ ይዘት አላቸው ተብለው የሚገመቱትን ባሕረ ሰላጤዎችና ወንዞችን በሚመለከት ረገድ በዓለም አቀፍ ስምምነቱ ከአንቀጽ ፫፻፴፪-፫፻፴፯ የተደነገጉት ሕጎች "በተባበሩት ኃያላን መንግሥታት (አላይድ ኤንድ አሶስየትድ ፓወርስ) በሚደረገው እና በመንግሥታት ሕብረት (ሊግ ኦፍ ነሽንስ) በሚጸድቀው ዓለም አቀፍ ስምምነት ሕግ ሊተኩ እንደሚችሉ እና ይህ ዓለም አቀፍ ስምምነት በተለይ በኦደር ወንዝና በሌሎችም ተፈጻሚነት እንደሚኖረው ይደነግጋል ።

ቀጽ ፫፻፴፰ትን መሠረት በማድረግ ነገሩን ብናየው እንኳ ፣ የቫርሰሎና አለም አቀፍ ስምምነትን ማጽደቅ አስፈላጊ አይሆንም ለማለት ስለማይቻል የቫርሰሎና ዓለም አቀፍ ስምምነት ሳይጸድቅ በቨርሳይ ዓለም አቀፍ ስምምነት አንቀጽ ፫፻፴፰ የተደነገጉትን ውጤቶች ያስከትል ማለት አይቻልም"[7] ሲል ወስኗል ።

በተመሳሳይ "በአፐር ሳቮይ ፍሪ ዞንስ እና በጀክስ ወረዳ ጉዳይ" ቋሚው ፍርድ ቤት ፍሬ ዞንስን ለማስ ቀረት የተደረገው የቨርሳይ ዓለም አቀፍ ስምምነት ክፍል ፪ ፣ አንቀጽ ፬፻፴፭ ፤

"ስዊትዘርላንድ በስምምነቱ ስላልተካፈለች ከስም ምነቱ በኋላ የፈቀደችውን ግዴታ በሚመለከት አንፃር ካልሆነ በስተቀር ስምምነቱ ሊፈጸምባት አይችልም"[8] በማለት ወስኗል ።

ማክስ ሁበር የተባሉት ዳኛ ፖልማስ ደሴት በተ ባለው ስፓኝ ከሌሎች አገሮች ጋር ባደረገችው ዓለም አቀፍ ስምምነት ስፓኝ በፖልማስ ደሴት ያላትን መብት ሌሎች አገሮች አውቀውላታል በማለት የቀረበላቸውን ክርክር መርምረው በሰጡት ውሳኔ ፤

"የስምምነቱ ትክክለኛ አተረጓጐም ምንም ቢሆ ንም ፣ የሦስተኛ ነፃ አገሮችን መብቶች ያስቀራል ብሎ መተርጎም እንደማይቻል ግልጽ ነው ። 'ፊሊፒንስ' የስፓኝ ግዛት መሆኗን በማረጋገጥ ስፓኝ ከሦስተኛ አገሮች ጋር የፈጸመቻቸው ስምምነቶች በኔዘርላንድስ ላይ ተፈጻሚ ሊሆኑ እንደማይችሉም ግልጽ ነው"[9] በማለት ይህን መሠረተ ሐሳብ በመከተል ወስነዋል ።

የሐርባርድ ምርምር (ሪሰርች) ስምምነቶችን በሚመ ለከት ረገድ ይህን ተቀባይነት ያገኘውን የዓለም አቀፍ ሕግ እንደሚከተለው ገልጾታል ፣ "አንድ ስምምነት በስምምነቱ ተካፋይ ባልሆነ አገር ላይ ግዴታን ሊያስ ከትል አይችልም" ።[10]

በአሁኑ ዓለም አቀፍ ሕግ "ፓክታ ተርቲስ ነክ ኖሰ ንት ነክ ፕሮሱንት" በሌሎች አገሮች የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ አለመግባት ከሚለው ሐሳብ ጋር በቀጥታ የተ ያያዘ ነው ።[10(ሀ)]

በዓለም አቀፍ ሕግ ኮሚሽን በተዘጋጀው ረቂቅ[11] የተ መሠረተው እ ኤ አ በ፲፱፻፷፱ ዓ/ም የወጣው ስምምነ ቶችን ስለሚመለከት ሕግ የቭየና ዓለም አቀፍ ስምም ነት (ኮንቬንሽን) አንቀጽ ፴፬ እንደሚከተለው ይደነ ግጋል ፦

"አንድ ስምምነት በሦስተኛ አገር ፈቃድ ካልሆነ በቀር መብትም ሆነ ግዴታ ሊያስከትል አይችልም ።"

የዓለም አቀፍ ኮሚሽን እ ኤ አ በ፲፱፻፷፬ ዓ/ም ለዚህ አንቀጽ ለጊዜው ሰጥቶት የነበረውን "የስምምነቶች ውጤት በተስማሚ ወገኖች ላይ ብቻ ተፈጻሚነት እን ዲኖራቸው የሚያዝ ጠቅላላ ሕግ" የሚለውን ርዕስ በመጨረሻ "ሦስተኛ ብሔሮችን የሚመለከት ጠቅላላ ሕግ" በሚል ርዕስ ተክቶታል ። እንደዚሁም ይህ "አንድ ስምምነት ተፈጻሚነት የሚኖረው በተስማሚዎቹ ወገ ኖች መካከል ብቻ ነው " ተብሎ ተደንግጎ የነበረ ውን አንቀጽ ለግለሰቦች ተፈጻሚነት አይኖረውም ወደ ሚል ያልሆነ ግምት እንዳያመራ በማሰብ ከላይ በተጠ ቀሰው አንቀጽ ተተክቷል ።

"ፓክታ ተርቲስ ነክ ኖሰንት ነክ ፕሮሱንት" የሚ ለው መርህ በዓለም አቀፍ ሕግ የተለየ ሁኔታን በሚመ ለከት ረገድ ተፈጻሚነት ይኖረዋል ወይስ አይኖረ ውም ? የሚለው ጥያቄ ሁልጊዜ አከራካሪ ነበር ። ኮሚ ሽኑንም በሐሳብ የከፋፈለው ይኸው ነጥብ ነበር ። ዓለም አቀፍ ስምምነቶች ተካፋይ ባልሆኑ ወገኖች ላይ ግዴ ታን የማያስከትሉ በመሆናቸው ፣ ግዴታን በሚመለከት ረገድ መርሁ ምን ጊዜም ቢሆን ተፈጻሚ ነው በሚለው ሐሳብ ላይ የኮሚስዮኑ አባላት ሙሉ በሙሉ የተስማሙ ሲሆን በሐሳብ የተለያዩት ዓለም አቀፍ ስምምነቶቹ ተካፋይ ላልሆኑ ወገኖች መብት ያስገኛሉ ወይስ አያስ ገኙም በሚለው ጥያቄ ላይ ነበር ።

በዚህ መሠረተ ሐሳብ ላይ የተመሰረተ ሳይሆን አን ዳንድ ጊዜ ዓለም አቀፍ ስምምነቶች ባልተካፈሉባቸው

---

7 ፒ ሲ አይ ጀ ፓብሊከሽንስ (እ ኤ አ ፲፱፻፳፱) ሲርይስ ኤ ፣ ቁ 23 ፣ ገጽ 21 ።

8 ከላይ የተጠቀሰው (እ ኤ አ ፲፱፻፴፪) ሲርይስ ኤ/ቢ ፣ ቁ 46 ፣ ገጽ 141 ።

9 ሪፖርትስ ኦፍ ኢንተርናሽናል አርቢትራል አዋርድስ ፣ (የተባበሩት መንግሥታት እትም) ቮልዩም 2 ፣ ገጽ 31 ።

10 "ሪሰርች ኢን ኢንተርናሽናል ሎው ኦፍ ትሪቲስ" አሜሪካን ጆርናል ኦፍ ኢንተርናሽናል ሎው ፤ (እ ኤ አ ፲፱፻፴፭) 29 ቮልዩም ማሟያ (ሳፕሊመንት) ።

10(ሀ) ኢንሳይክሎፒድያ ፕራዋም የድዝይና ርዶወን ኤ ስቶሉንከው ም ድዝይናሮድ ውይች (የዓለም አቀፍ ሕግና ግንኙነት ኢንሳይክሎፒድያ) ፣ (ዋርሰው እ ኤ አ ፲፱፻፸፮) ፣ ገጽ 253 ።

11 ዓለም አቀፍ ስምምነቶችና ሦስተኛ ብሔሮችን በሚመለከት ረገድ በተባበሩት መንግሥታት የዓለም አቀፍ ሕግ ኮሚሽን የቭየናው ዓለም አቀፍ ስምምነትን ባዘጋጀበት ጊዜ የተደረገውን ከፍተኛ ጥናት መጥቀሱ አስፈላጊ ነው ። ኮሚሽኑ እ ኤ አ በ፲፱፻፵፱ ዓ/ም ባደረገው የመጀመሪያ ስብሰባው የዓለም አቀፍ ስምምነቶች ሕግጋት በሕግ ለመቀረጽ (ኮዲፊኬሽን) አመቺ ናቸው በማለት ከገለጻቸው ሕግጋት አንዱ ነበር ። ነገር ግን ፣ ኮሚሽኑ በሥራ ብዛት ምክንያት እስከ እ ኤ አ ፲፱፻፷ ዓ/ም ድረስ ምንም ለማድረግ አልቻለም ነበር ። እ ኤ አ በ፲፱፻፷፩ ዓ/ም ባደረገው አሥራ ሦስተኛ ስብሰባው ፣ ኮሚሽኑ በፊት መርጧቸው በነበረው አዘጋጆች በተጠቆመው መሠረት የተቀረጸ ሕግ (ኮድ) ከማዘጋጀት ይልቅ ተስማሚ ለሆነ ኮንቬንሽን (ስምምነት) መሠረት የሚሆን የዓለም አቀፍ ስምምነት ሕግ በሰር ሐምፈሪ ዋልዶክ ኃላፊነት እንዲዘጋጅ ወሰነ ። በአሥራ አራተኛው (እ ኤ አ በ፲፱፻፷፪ ዓ/ም) ፣ በአሥራ አምስተኛው (እ ኤ አ በ፲፱፻፷፫ ዓ/ም) እና በአሥራ ስድስተኛው (እ ኤ አ በ፲፱፻፷፬ ዓ/ም) ስብሰባው ኮሚሽኑ በአዘጋጁ በቀረበለት ሪፖርት መሠረት ዓለም አቀፍ ስምምነቶችን ከሚመለከተው ሕግ የመጀመሪያዎቹን ሦስት ክፍሎች አጸደቀ ። መንግሥታት ያቀረቡለትን አስተያየቶች መሠረት በማድረግ ፣ ኮሚሽኑ ክፍሎቹን ንኡስ ክፍሎቹንና የአንቀጾቹን ቅደም ተከተል በማሻሻል የመጨረሻውን የዓለም አቀፍ ስምምነቶች ሕግ እ ኤ አ በ፲፱፻፷፮ ዓ/ም አጸደቀ ። በዚህ ጉዳይ ፣ ሪፖርት ዘ ኢንተርናሽናል ሎው ኮሚሽን ኦን ዘ ወርክ ኦፍ ኢትስ ኤይቲንዝ ሰሽን (የዓለም አቀፍ ረቂቅ ሕግ ኮሚሽን አሥራ ስምንተኛ ስብሰባ ዘገባ)— ጀኔቭ—ሜይ4—ጁላይ29፣ ፲፱፻፷፮ ዓ/ም ድራፍት አርቲክል ኦን ዘ ሎው ኦፍ ትሪቲስ—ጀኔቭ ኤኤስ ኦፍ ሬክ 21 ፣ ሳፕሊ (ማሟያ) ቁ 9 በኤ/6309 /ሪቭ 1/ ይመለከቷል ። እነዚህ ረቂቅ አንቀጾች እ ኤ አ በ፲፱፻፷፰-፲፱፻፷፱ በቭየና ለተደረገው ዲፕሎማቲክ ስብሰባ መሠረት ሆነው የዓለም አቀፍ ስምምነቶች ሕግ ስምምነት አዘል በሆነ መልክ ተረቀቀ ።

ሦስተኛ አገሮች ላይም በአንዳንድ ሁኔታዎች ተፈጻሚነት እንዳላቸው አያከራክርም ። አከራካሪ የሚሆነው እነዚህ ልዩ ሁኔታዎች ተቀባይነትና ሕጋዊነት የሚኖራቸው በምን ዓይነት ጉዳዮችና እስከምንስ ድረስ ነው የሚለው ነጥብ ነው ። በመሠረቱ እነዚህ የተለዩ ሁኔታዎች በሁለት ሊከፈሉ ይችላሉ ፤ እነዚህም ፥ ፩/በሦስተኛ አገሮች ላይ ግዴታዎችን የሚያስከትሉ ዓለም አቀፍ ስምምነቶች (ፓክታ ኢን ደትሪመንቱም ተርቲ) ፥ እና ፪/ ለሦስተኛ አገሮች መብቶችን የሚያስገኙ ዓለም አቀፍ ስምምነቶች (ፓክታ ኢን ፋቮሬም ተርቲ) ናቸው ።

እነዚህን ሁለት ሁኔታዎች ከማየታችን በፊት ፥ ከነዚህ ሁለት ሁኔታዎች ውጭ ዓለም አቀፍ ስምምነቶች በሦስተኛ አገሮች ላይ ተፈጻሚ የሚሆኑባቸውን ሁኔታዎች መመርመር አስፈላጊ ይሆናል ።

ለምሳሌ ተስማሚዎቹ አገሮች በፊት ሰጥተውት ከነበረ ይበልጥ ጥቅም የሚሰጡ አንቀጾች የያዘ የንግድ ዓለም አቀፍ ስምምነት ከተስማሚዎቹ አገሮች ጋር በሌላ ስምምነት ከሁሉም በበለጠ የመታየት መብት (ሞስት ፌቨርድ ኔሽን ክሎዝ) ባገኙ ሦስተኛ አገሮችም ተፈጻሚ ይሆናል ። ነገር ግን እነዚህን አገሮች በሙሉ በተዘዋዋሪ መንገድ የሚያያይዝ ተቀባይነት ያገኘ ሁኔታ አለ ። በመሆኑም "ሦስተኛ አገር ማለት በዓለም አቀፍ ስምምነት ያልተካፈለ አገር ማለት ነው"[12] የሚለውን በቬየና ስምምነት የሚገኘውን ጠቅላላ ሕግ አይከተልም ።

አንዳንድ ጊዜ ደግሞ አንድ አገር ምንም እንኳን በአንድ ዓለም አቀፍ ስምምነት ተካፋይ ባይሆንም በሌላ ዓለም አቀፍ ስምምነት ግዴታውን ከተቀበለ ያልተካፈለበትን ስምምነት ማክበር ይኖርበታል ። ለምሳሌ "የፖላንድ ዜጎችን አያያዝ በዳንዚግ" በሚለው ጉዳይ ቋሚው ፍርድ ቤት በቨርሳይ ዓለም አቀፍ ስምምነት ክፍል ፫ አንቀጽ ፩፻፬ አንፃር የዳንዚግ ነፃ ከተማን አቋም መርምሯል ፤ ምንም እንኳን የዳንዚግ ነፃ ከተማ በስምምነቱ ባትካፈልም በሌሎች ነፃ ከተማዋን እና በሷ እና በፖላንድ የሚኖረውን ሕጋዊ ግንኙነት ባቋቋሙት ሰነዶች ስምምነቱን እንደተቀበለችው ተቆጥራለች ። ፍርድ ቤቱ በሐሳቡ ማጠቃለያ "ነፃዋ ከተማ ፥ ዋናዎቹ ቃል ኪዳን የገቡ ኃያላን አገሮች በቨርሳይ ዓለም አቀፍ ስምምነት አንቀጽ ፩፻፬ መሠረት በመደራደር የደረሱበትን ስምምነት መቀበሏ እርግጠኛ በመሆኑ አንቀጹን መቀበሏ አያጠራጥርም"[13] በማለት ወስኗል ።

## በሦስተኛ አገሮች ላይ ግዴታዎችን የሚያስከትሉ ዓለም አቀፍ ስምምነቶች (ፓክታኢን ደትሪመንቱም ተርቲ)

በአጠቃላይ አነጋገር ያለ አንድ ሦስተኛ አገር ፈቃድ ዓለም አቀፍ ስምምነቶች መብትም ሆነ ግዴታ ሊያስከትሉ አይችሉም የሚለውን ሕግ በማስፋፋት የቬየና ዓለም አቀፍ ስምምነት (ኮንቬንሽን) በሦስተኛ አገሮች ላይ ግዴታን ስለሚያስከትሉ ዓለም አቀፍ ስምምነቶች የሚከተለውን መሠረተ ሐሳብ አስፍሯል ፦ "አንድ ዓለም አቀፍ ስምምነት በሦስተኛ አገር ላይ ግዴታን የሚያስከትለው ስምምነቱን የመሠረቱት አገሮች ስምምነቱ በሦስተኛ አገር ግዴታን እንዲያስከትል ሐሳብ ሲኖራቸው እና ሦስተኛው አገርም ግዴታውን በማያሻማ ሁኔታ በጽሑፍ ሲቀበለው ነው ።"[14]

ይህ ሕግ በስምምነቱ ተካፋይ ያልሆነ ሦስተኛ አገር በስምምነቱ ተገዳጅ ከመሆኑ በፊት መሟላት ያለባቸውን የሚከተሉትን ሁለት ሁኔታዎች ይደነግጋል ፦

፩/ ተስማሚዎቹ አገሮች አግባብ ባለው የስምምነቱ ክፍል በስምምነቱ ተካፋይ ባልሆነው አገር ግዴታ እንዲመሠረት ማድረግ ፥ እና

፪/ በስምምነቱ ተካፋይ ያልሆነው ሦስተኛው አገር ግዴታውን ለማክበር በማያሻማ ሁኔታ መስማማት ።

ይህም ዓለም አቀፍ ስምምነቱን በመጀመሪያ በተፈራረሙት አገሮች እና በሦስተኛው አገር ተጨማሪ ስምምነት መኖር እንዳለበት ያሳያል ። በዚህ አንፃር ሲታይ የሦስተኛው አገር ግዴታ ሕጋዊ መሠረቱ ዓለም አቀፍ ስምምነቱ ሳይሆን ተጨማሪው ስምምነት ይመስላል ። የሆነ ሆኖ ሁኔታው የሚያሳየው ዓለም አቀፍ ስምምነቱ ተካፋይ ባልሆነበት አገር መፈጸሙን ነው ።

የሕጉን አሠራር በይበልጥ ለመረዳት ቋሚው ፍርድ ቤት በፍሪዞንስ ጉዳይ የቨርሳይ ስምምነት አንቀጽ ፬፻፴፭ትን በማስመልከት የወሰደውን አቋም መመርመር ይጠቅማል ። ስዊትዘርላንድ በቨርሳይ ስምምነት አልተካፈለችም ። ነገር ግን ስምምነቱ ከመፈረሙ በፊት በስምምነቱ አንቀጽ ፬፻፴፭ ትስማማ እንደሆን በፈረንሳይ መንግሥት ተጠይቃ ነበር ። የስዊትዘርላንድ ፌዴራል ምክር ቤትም አንዳንድ ሁኔታዎች ከተሟሉ አንቀጽ ፬፻፴፭ትን ስዊትዘርላንድ እንደምትስማማበት ገልጾ ነበር ። ስዊትዘርላንድ በአንቀጹ ይዘት ካልተስማማችባቸው ምክንያቶች አንዱ የድሮዎቹ ዓለም አቀፍ ስምምነቶች በጊዜው ከነበረው ተጨባጭ ሁኔታ አብረው አይሄዱም[15] የሚል ይገኝበታል ፤ ፈረንሳይ የዱሮዎቹ ዓለም አቀፍ ስምምነቶች በአንቀጽ ፬፻፴፭ ተሽረዋል በማለት ያቀረበችውን ክርክር ፍርድ ቤቱ አል

---

12 የቬየና ዓለም አቀፍ ስምምነት (ኮንቬንሽን) አንቀጽ ፪ እና ፩ (ኤች) ።

13 ፒ ሲ አይ ጀ ፓብሊከሽንስ (እ ኤ አ ፲፱፻፴፪) ፥ ሲሪይስኤ ቢ ፥ ቁ 44 ገጽ 30 ።

14 አንቀጽ ፴፬ ።

15 ማለትም የፍሪ ዞንስ ከጊዜው ተጨባጭ ሁኔታ ጋር አብሮ ያለመሄድና መሻሩን በማረጋገጥ ።

ተቀበለውም ። ያልተቀበለበትም ምክንያት ስዊትዘርላንድ አንቀጽ ፩፻፴፮ትን ሙሉ በሙሉ አልተቀበለችውም በማለት ነበር ። ፍርድ ቤቱ "ስዊትዘርላንድ በቨርሳይ ስምምነት ያልተካፈለች ስለሆነ በተቀበለችው መጠን ካልሆነ በቀር አንቀጽ ፩፻፴፮ በስዊትዘርላንድ ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም ፤ ስዊትዘርላንድ አንቀጽ ፩፻፴፮ትን እስከ ምን ያህል እንደተስማማችበት የሚወስነው በሜይ ፳ ቀን ፲፱፻፲፱ ዓ/ም ለፈረንሳይ የላከችው ማስታወሻ ነው ። ምክንያቱም የስዊስ መንግሥት አንቀጽ ፩፻፴፮ትን "ተቀብሎታል" ማለት የሚቻለው በዚህ ማስታወሻ በተገለጹት ገደቦች መሠረት ነው"[16] በማለት በፍርድ ሐተታው ገልጾታል ።

አንድ ዓለም አቀፍ ስምምነት በሦስተኛ አገር ላይ ኃላፊነትን ወይም ተስማሚ ያልሆኑ ግዴታዎችን መመሥረት ይችላል ። ለምሳሌ ተስማሚዎቹ አገሮች በራሳቸው ላይ እንደዚህ ዓይነቶቹን ግዴታዎች ከመሠረቱ በኋላ ሦስተኛ ብሔሮች በተመሳሳይ ሁኔታ በግዴታዎቹ እንዲስማሙባቸው እንደሚጥሩ ቃል የሚገቡበት ጊዜ ሊኖር ይችላል ። የተባበሩት መንግሥታት ቻርተር አንቀጽ ፪ የሚደነግገውም እንዲህ ዓይነቱን ሁኔታ ነው ። የአንቀጹ ይዘት የሚከተለው ነው ፦ "ዓለም አቀፍ ሰላምንና ፀጥታን ለመጠበቅ አስፈላጊ በሆነው መጠን የተባበሩት መንግሥታት አባል ያልሆኑ አገሮች እነዚህን መሠረታዊ ዓላማዎች[17] በመከተል እንደሚተባበሩ ጽሕፈት ቤቱ የማረጋገጥ ግዴታ አለበት ።"

የአንታርክቲክ ዓለም አቀፍ ስምምነትም (በዲሰምበር ፩ ቀን ፲፱፻፶፱ ዓ/ም በዋሺንግቶን ከተማ የተፈረመ) ተመሳሳይ ድንጋጌ ያለው አንቀጽ ይገኝበታል ። በዚህ ስምምነት መሠረት ተዋዋዮቹ ወገኖች "በስምምነቱ የተገለጹትን መሠረታዊ ዓላማዎች የሚፃረሩ ድርጊት ማንም ሰው እንዳይፈጽም አስፈላጊውን ጥረት ለማድረግ" ተስማምተዋል ። ይህ አንቀጽ በተጨማሪ ተስማሚዎቹ ወገኖች የሚያደርጉት "ተገቢው ጥረት" "ከተባበሩት መንግሥታት ቻርተር ጋር" የማይቃረን መሆን እንዳለበት መደንገጉ ሳይገለጽ መታለፍ የለበትም ። ይህን ገደብ የአንታርክቲክ ዓለም አቀፍ ስምምነትና የተባበሩት መንግሥታት አባል ያልሆነ አገር እንዴት ይመለከተው ይሆን ? የሚል ጥያቄ ያስነሳል ።

ሦስተኛ አገር በቀጥታ የገባበት ግዴታ ባይኖርም ተስማሚዎቹ አገሮች የሚፈጽሙት ድርጊት ሕገ ወጥ እስካልሆነ ድረስ ፣ ሦስተኛው አገር የሚፈጽማቸው ድርጊቶች የስምምነቶቹ ተፃራሪ አለመሆናቸውን የማረጋገጥ ግዴታቸውን ለመወጣት የሚከለክላቸው ነገር አይኖርም ። ሆኖም እንደዚህ ዓይነቱ ዓለም አቀፍ ስምምነት በሦስተኛው አገር ላይ ግዴታ እንደማይመሰርት መታወቅ አለበት ።

ሌላው መታየት ያለበት ሁኔታ በፀብ አጫሪ አገር ላይ ግዴታን የሚመሠርት ዓለም አቀፍ ስምምነት ነው ። ለዚህ ሁኔታ ጀርመንን በሚመለከት እንፃር የፓትስዳም ዓለም አቀፍ ስምምነት መጥቀሱ ጠቃሚ ይሆናል ። በኮሚሽኑ ውይይት ስምምነቱ በፀብ አጫሪ አገር ላይ ተፈጻሚ የመሆኑ ጉዳይ አጠያያቂ ሆኖ ነበር ። ኮሚሽኑ የፀብ አጫሪ አገር ጉዳይ የስምምነቱን መሠረተ ሐሳብ አይመለከተውም የሚል አቋም ወስዷል ። በዚህ ጊዜ ኮሚሽኑ በዓለም አቀፍ ስምምነቱ ረቂቅ አንቀጽ ፵፱ መሠረት የአንድ አገር ፈቃደኛነት በኃይል ወይም በማስፈራራት ሲገኝ ውጤት የማይኖረው በማስገደድ የተገኘው ፈቃድ "የተባበሩት መንግሥታት ቻርተርን መሠረተ ሐሳብ የሚፃረር ድርጊት ለማስፈጸም ሲሆን ብቻ ነው"[18] በሚል ሐሳብ ተስማምቷል ስለዚህ በፀብ አጫሪ አገር ላይ በግድ ተፈጻሚ የሚሆን የዓለም አቀፍ ስምምነት አንቀጽ ከተባበሩት መንግሥታት ቻርተር መሠረተ ሐሳቦች ጋር የማይፃረር ከሆነ ሕጋዊ ስለሚሆን የኮሚሽኑን ዓለም አቀፍ ስምምነት ረቂቅ አንቀጽ ፵፱ኝን አይፃረርም ። ኮሚሽኑ የአንዳንድ መንግሥታትን ማሳሰቢያ በመከተል ፀብ አጫሪ አገርን በሚመለከት ረገድ በቻርተሩ መሠረት በሚወሰዱት እርምጃዎች አንዳንድ ግዴታዎች በፀብ አጫሪ አገር ላይ ተፈጻሚ እንዲሆኑ ቻርተሩ ስለሚደነግግ እነዚህን ግዴታዎች በሚመለከት አንፃር የሦስተኛው አገር ፈቃድ እንደማያስፈልግ የሚደነግግ አጠቃላይ በሆነ ይዘት የተዘጋጀ ንድፈ ሐሳብ በረቂቁ አንቀጽ ፸ ሆኖ እንዲጨመር ወሰነ ።[19]

ሦስተኛ አገርን የሚመለከቱ ዓለም አቀፍ ግዴታዎች የመሰረዝን ወይም የማሻሻልን ሁኔታ በቬየና ስምምነት (ኮንቬንሽን) እንደሚከተለው ተደንግጓል ፦

"የተስማሙት በሌላ አኳኋን መሆኑ ካልተረጋገጠ በቀር ፣ ግዴታው ሊሰረዝ ወይም ሊሻሻል የሚችለው በተስማሚዎቹ አገሮችና በሦስተኛው አገር ፈቃድ ብቻ ነው ።"[20]

ግዴታውን ለመሰረዝ የፈለገው ሦስተኛው አገር እስከ ሆነ ድረስ ይህ ሕግ በትክክለኛ አቋም የተመሠረተ ይመስላል ። ነገር ግን ግዴታውን ለመሠረዝ የፈለጉት ተስማሚዎቹ ወገኖች ከሆኑ የሦስተኛውን አገር ፈቃድ የማግኘቱ ጉዳይ ቀላል አይሆንም ። ተዋዋዮቹ ወገኖች ግዴታውን የማስፈጸም መብታቸውን ለመተው በሚወስኑበት ጊዜ የሦስተኛው አገር ፈቃድ መጠየቅ አለበት ማለቱ ትክክለኛ ላይሆን ይችላል ። ሆኖም እንደዚህ ዓይነቱ ሁኔታ በሚያጋጥምበት ጊዜ ችግር የመኖሩ ዕድል በጣም የመነመነ ነው ። የዓለም አቀፍ ሕግ ኮሚሽን ይህን አቋም የወሰደው በዓለም አቀፍ ግንኙነት እንደዚህ ዓይነቶቹ ቀላል ሁኔታዎች በጣም

---

16 ፒ.ሲ.አይ.ጀ ፓብሊኬሽንስ (እ.ኤ.አ ፲፱፻፳፱) ፣ ሲርይስ ኤ ፣ ቁ22 ገጽ 17-18 እና (እ.ኤ.አ ፲፱፻፴፪ ዓ/ም) ፣ ሲርይስ ኤ/ቢ ፣ ቁ46 ፣ ገጽ 141 ።

17 በተባበሩት መንግሥታት ቻርተር በአንቀጽ ፪ እንደተደነገገው ።

18 የቬየና ዓለም አቀፍ ስምምነት (ኮንቬንሽን) አንቀጽ ፶፪ " - - በተባበሩት መንግሥታት ቻርተር የተደነገጉትን የዓለም አቀፍ ሕግ መሠረተ ሐሳቦች መጣስ")

19 የቬየና ዓለም አቀፍ ስምምነት (ኮንቬንሽን) አንቀጽ ፸፭ ፣ "ፀብ አጫሪ አገር በተባበሩት መንግሥታት ቻርተር መሠረት ስለ ፀብ አጫሪነቷ በዓለም አቀፍ ስምምነት የሚወሰኑባት ግዴታዎች እንደተጠበቁ ይሆናሉ ።"

20 አንቀጽ ፴፯(፩) ።

ጥቂቶች ናቸው ፤ አብዛኛውን ጊዜ የሦስተኛ አገር ግዴታ የበለጠ ጥልቀትና ክብደት ያዘለ ግንኙነትን የሚመለከት ስለሚሆን ማንኛውም የግዴታ ለውጥ በጋራ ስምምነት መደረግ አለበት ከሚል እምነት የተነሳ መሆን አለበት ።

## ለሦስተኛ አገሮች መብቶችን የሚያስከትሉ ዓለም አቀፍ ስምምነቶች (ፓክታ ኢን ፋቮረም ተርቲ) ።

ከላይ እንደተገለጸው ሁሉ ግዴታዎችን በሚመለከት ረገድ የሦስተኛ አገር ስምምነት ምንጊዜም ቢሆን አስፈላጊ ለመሆኑ በኮሚሽኑ ሙሉ በሙሉ ስምምነት ቢደረስበትም ፥ አንድ ዓለም አቀፍ ስምምነት በስምምነቱ ተካፋይ ላልሆነ ሦስተኛ አገር መብት ያስገኛል ወይስ አያስገኝም ? በሚለው ጥያቄ ላይ የሐሳብ ልዩነት ተፈጥሮ ነበር ። ከኮሚሽኑ አባሎች ከፊሎቹ መብትን በሚመለከት ረገድ ተስማሚዎቹ አገሮች እስከፈቀዱ ድረስ ዓለም አቀፍ ስምምነቱ ተስማሚ ባልሆነው ሦስተኛ አገር ላይ መብት ለመፍጠር ይችላል ፤ ነገር ግን ተስማሚ ያልሆነው ሦስተኛው አገር መብቱን የመቀበል ወይም በመብቱ የመጠቀም ግዴታ አይኖርበትም የሚል አቋም ነበራቸው ።

ይህ የሐሳብ ልዩነት የመነጨው ለሦስተኛ አገሮች ጥቅም ስለሚደረጉ ውለታዎች በዓለም አቀፍ ሕግ ምሁራን መካከል በነበረው የሐሳብ ልዩነት ነው ። ዓለም አቀፍ ስምምነቶች ለሦስተኛ አገሮች ጥቅም የሚሰጡ ገደቦች ሲይዙ እንደሚችሉ በምሁራኑ መካከል ስምምነት ቢኖርም ፥ ሦስተኛው አገር የመብቱ ባለቤት ለመሆን ስምምነቱን ማጽደቅ አለበት ወይስ የለበትም ? በሚለው ጥያቄ የአቋሙ ልዩነት እስከ አሁን ድረስም አለ ።

ለምሳሌ ያህል ለሦስተኛ አገር ጥቅም የሚደረግ ገደብ ሦስተኛው አገር እንዲቀበል ከሚቀርብ ውል ያልተለየ ፥ ተፈጻሚ እንዲሆንም የሦስተኛውን አገር መቀበል የሚጠብቅ ድርድር ነው ፤ ሦስተኛው አገር ሲቀበለውም ሁለተኛ ስምምነት ተደርጓል ማለት ነው ። ከዚህ ስምምነት በኋላም ሦስተኛው አገር ተዋዋይ ወገን እንጂ ሦስተኛ አገር ነው ለማለት አይቻልም የሚል አቋም ነበር ። ይህም አቋም ንጉለስኮ በሚባሉ ዳኛ በፍሬዞንስ ጉዳይ እንደሚከተለው ተገልጾአል ፦

"የዓለም አቀፍ ስምምነት (ኮንቬንሽን) ለሦስተኛ አገር መብት የያዘ ሊሆን ይችላል ። ነገር ግን በአንድ አገር ሕግ የአንድ ሦስተኛ ወገን መብት የሚመነጨው ከስምምነቱ አንቀጾች ሲሆን ፥ በዓለም አቀፍ ሕግ መሠረት ግን ተዋዋዮቹ አገሮች መብት ከተሰጠው ሦስተኛ አገር ጋር የመጀመሪያው ዓለም አቀፍ ስምምነት ክፍለ አካል የሚሆን ተጨማሪ ስምምነት ለማድረግ በጋራ ግዴታ ይገባሉ ።"[21]

ነገር ግን ደ አረካርጋ እንዳሉት ፤

"ይህ የውል ማቅረብ ጽንሰ ሐሳብ ከሃምሳ ዓመት በፊት የፍትሐ ብሔር ምሁራን ስቲፑላስዮን ኢን ፋቮረም ተርቲ የሚባለውን ፅንሰ ሐሳብ በሁለት ተከታታይ ውሎች ለመግለጽ የሰነዘሩት ሐሳብ ነው ። ይህ ጽንሰ ሐሳብ በዓለም አቀፍ ሕግ ተቀባይነት ሊኖረው አይገባም ፤ ምክንያቱም ጥቅምን መቀበል ሁለተኛ ውል መዋዋል ነው ማለት አይቻልም ።"[22]

ይህ ውልን መቀበል ሊባል አይቻልም ። ሦስተኛው አገር መፈጸም ያለበት ድርጊት ለሁለተኛ ስምምነት የሚያስፈልግ ፈቃድ መስጠት ሳይሆን በዓለም አቀፍ ስምምነት ያለውን መብት መቀበል ብቻ ነው ። ሦስተኛው አገር በመብቱ የመጠቀም ወይም መብቱን ላለመቀበል ያለው መብት የተጠበቀ ነው ስለዚህ ስምምነቱን መቀበል በዚህ አንጻር ሲታይ ፥ ተጠቃሚው መብቱን እንዳልናቀው የሚያስቆጥር ድርጊት ብቻ ይሆናል ።[23]

የቬየና ስምምነት (ኮንቬንሽን) "አንድ ዓለም አቀፍ ስምምነት ሦስተኛው አገር ካልፈቀደ በስተቀር መብት አያስገኝለትም" የሚለውን አንቀጽ ፴፬ትን በማስፋፋት ግዴታዎችን በሚመለከት ረገድ ካለው አቋም ለየት ያለ አቋም ይዞአል ። በዚህም መሠረት የስምምነቱ አንቀጽ ፴፮ የመጀመሪያው አዲስ መስመር ተቃራኒ ሐሳብ ካልተገለጸ በስተቀር የሦስተኛው አገር ፈቃድ እንደተሰጠ ይቆጠራል በማለት ይደነግጋል ። ኮሚሽኑ የአንቀጹ ይዘት ይህ እንዲሆን የመረጠበት ምክንያት መብቱ የተሰጠው በአጠቃላይ አገሮችን ለመጥቀም ወይም የተወሰኑ አገሮችን ለመጥቀም በሚሆንበት ጊዜ ሕጉን በቀላሉ ሥራ ላይ ለማዋል እንዲቻል በማሰብ ነው ።

ኮሚሽኑ እንደተገነዘበው ሁሉ ተጠቃሚዎቹ አገሮች የተለያዩ ሊሆኑ ይችላሉ ፥ በቬርሳይ ዓለም አቀፍ ስምምነት ስዊትዘርላንድን[24] እና ዴንማርክን[25] ለመጥቀም እንደተደረገው ሁሉ አንዳንድ ጊዜም በገደብ መጠቀም የሚችሉ አገሮች የተወሰኑ ሊሆኑ ይችላሉ ። ከሁለተኛው ዓለም ጦርነት[26] በኋላ በተደረጉት የሰላም ዓለም አቀፍ ስምምነቶች እንደሚታየው ደግሞ አንዳንድ ጊዜ የገደቡ ተጠቃሚዎች የተወሰኑ አገሮች ሲሆኑ

21 ፒ. ሲ. አይ. ጀ. ፓብሊከሽንስ (እ. ኤ. አ ፲፱፻፷፱) ፥ ሲርይስ ኤ ቁ 22 ፥ ገጽ 36-37

22 ኢ. ጀ. ደ. አሬካጋ ፥ "ትርቲ ስቴፑሌሽንስ ኢን ፌቨር ኦፍ ተርድ ስቴትስ" ፥ አሜሪካን ጆርናል ኦፍ ኢንተርናሽናል ሎው ፥ (እ. ኤ. አ ፲፱፻፶፮) ፥ በልዩም 50 ፥ ገጽ 352 ።

23 "በዓለም አቀፍ ስምምነት የሚገኙ በስምምነቱ ሳልተካፈለ ሦስተኛ አገር ጥቅም የሚሰጡ አንቀጾች በሦስተኛው አገር ተቀባይነት ማግኘት አለማግኘታቸው የሚወሰነው በሦስተኛው አገር ነው" ከሚለው እ. ኤ. አ በፌብርዋሪ ፳ ቀን ፲፱፻፷፰ ዓ/ም ከተደረገው የሐባናው ስለ ዓለም አቀፍ ስምምነቶች ሕግ ስምምነት (ኮንቬንሽን) ከአንቀጽ ፱ ጋር ማነጻጸር ጠቃሚ ይሆናል ።

24 የቬርሳይ ዓለም አቀፍ ስምምነት አንቀጽ ፫፻፶፰ እና ፴፯ ።

25 የቬርሳይ ዓለም አቀፍ ስምምነት አንቀጽ ፩፻፱ ።

26 ከፊንላንድ (አንቀጽ ፰፱) ኢታሊ (አንቀጽ ፸፪) ፥ ቡልጋሪያ (አንቀጽ ፰፰) ፥ ሐንጋሪ (አንቀጽ ፴፱) እና ሩማንያ (አንቀጽ ፴) የተደረገትን የሰላም ስምምነቶች በአሜሪካን ጆርናል ኦፍ ኢንተርናሽናል ሎው ፤ (እ. ኤ. አ ፲፱፻፵፰) በልዩም 24 ፥ ሳፐሊመንት (ማሟያ) ይመለከቷል ።

ይችላሉ ። እነዚህ የሰላም ዓለም አቀፍ ስምምነቶች በጦርነቱ የተሸነፉ አገሮች በጦርነቱ ያገኙት ጥቅም በስምምነቶቹ ላልነበሩትና ጥቅሙ ለሚገባቸው አገሮች መልቀቅ እንደነበረባቸው ደንግገዋል ። የተባበሩት መንግሥታት ቻርተርም ፣ ለምሳሌ ያህል ፣ አባል ያል ሆኑ አገሮች የሚመለከታቸው እስከሆነ ድረስ በሴኩሪቲ ካውንሲል በሚደረገው በማንኛውም ያለመግባባት ውይይት እንዲካፈሉ (አንቀጽ ፴፪) ወይም አለመግባባቱን ያስከተሉት ነገሮች ለሴኩሪቲ ካውንሲል ወይም ለጠቅላላው ስብሰባ እንዲያቀርቡ (አንቀጽ ፴፭) መብት ይሰጣቸዋል ። በመጨረሻም ይህ ሦስተኛ አገሮችን ለመጥቀም የሚደረገው ገደብ ፣ በዓለም አቀፍ ወንዞች ባሕረ ሰላጤዎችና ክልሎች ትራንስፖርትን ስለማካሄድ ነፃነት[27] እንደተደነገገው ሁሉ መብቱን በአጠቃላይ ለብሔሮች መስጠትን ይመለከታል ።

እነዚህን ፍሬ ነገሮች በሚመለከት ረገድ የቬየና ስምምነት (ኮንቬንሽን) ለሦስተኛ አገሮች የሚሰጥ መብት "ለሦስተኛው አገር ለተወሰኑ ሦስተኛ አገሮች ወይም ለአገሮች በሙሉ"[28] እንዴት ሊመነጭ እንደሚችል ይደነግጋል ።

መብቱ የሚሰጣቸው አገሮች እንደሚፈቅዱ በመገመት ስምምነቱ ወሳኝ እድርጎ የሚቆጥረው የተስማሚዎቹ አገሮች የስምምነቱ አንቀጽ መብቱን እንዲያስገኝ በማቀድ መስማማት ነው ። "ከአንድ ዓለም አቀፍ ስምምነት ለሦስተኛ አገር መብት የሚመነጨው ተስማሚዎቹ አገሮች ሦስተኛው አገር መብት እንዲኖረው በማቀድ የተስማሙበት አንቀጽ ሲኖር ነው።"[29]

እንግዲህ ከስምምነቱ የሚመነጭ ከጥቅም ብቻ የተለየ ሕጋዊ መብት ለአንድ ሦስተኛ አገር ሲኖር የሚችለው ተስማሚዎቹ አገሮች ከላይ የተገለጸው ሐሳብ ሲኖራቸው ብቻ ነው ።

ሐሳቡን በሚመለከት ረገድ መደበኛው ዓለም አቀፍ ፍርድ ቤት እ ኤ አ በ፲፱፻፴፪ ዓ/ም በፍሪ ዞንስ ጉዳይ በሰጠው ፍርድም እንደሚከተለው ወስኗል ፦

"ሌሎች አገሮች በፈጸሙት ስምምነት የተገኘ መብት አለ ወይስ የለም ? የሚለው ጥያቄ መታየትና መወሰን ያለበት በያንዳንዱ ጉዳይ ነው ፤ ለሦስተኛ አገር ጥቅም ያዘለ ስምምነት የተስማሙት አገሮች መብቱ ተሰጥቶኛል ለሚለው አገር መብቱ እንዲያገለግል ያቀዱ ለመሆናቸውና አገሩም ይህን መብት ለመቀበሉ መረጋገጥ አለበት ።"[30]

የሐርባርድ ሪሰርች (ምርምር) አንቀጽ ፲፰ (ለ) ሦስተኛ አገር ጥቅም አለኝ ለማለት የሚችለው ጥቅሙ ይሰጠኛል የሚለው አንቀጽ የተደረገው "በግልጽ በስምምነቱ ላልተካፈለ ወይም ስምምነቱን ላላጸደቀ ሦስተኛ አገር ጥቅም እንዲሰጥ ታቅዶ ሲሆን ነው"[31] በማለት ይደነግጋል ።

በቬየና ስምምነት (ኮንቬንሽን) በአንቀጽ ፴፯፪ በዓለም አቀፍ ወንዝ ወይም ለመርከብ አገልግሎት በሚያገለግል ባሕረ ሰላጤ በምን ሁኔታ መጠቀም እንደሚቻል እንደተደነገገው ሁሉ ተጠቃሚው አገር በመብቱ መጠቀም የሚችለው በስምምነቱ ስለመብቱ አጠቃቀም የተደነገጉትን ገደቦች በመከተል መሆን አለበት ።[32]

እንደዚህ ዓይነት ገደቦች በስምምነቱ መኖር አለባቸው ወይም በስምምነቱ መሠረት መነደፍ አለባቸው ማለት ግን የተስማሚዎቹ አገሮች ለሦስቱኛ አገሮች የሰጡት መብት የማሻሻል ሥልጣናቸውን ይወስንባቸዋል ማለት ሊሆን አይችልም ።

የቬየናው ስምምነት (ኮንቬንሽን) እንደዚህ ዓይነቱ የማሻሻል ሥልጣን የተሰጡት መብቶችን እስከመሰረዝ ሊደርስ እንደሚችል ይደነግጋል ።

ተጠቃሚው አገር ሳይስማማበት ተስማሚዎቹ አገሮች በተከታይ ስምምነት መብት የሚሰጠውን የስምምነቱን አንቀጽ ለማሻሻል ወይም ለመሠረዝ ይችላሉ ወይስ አይችሉም ? ለሚለው ጥያቄ በዓለም አቀፍ ሕግ ምሁራን ሦስት የተለያዩ አቋሞች ነበሩ ።

አንደኛው ጠበብ ያለው አቋም ፣ ሦስተኛው አገር በስምምነቱ መጠቀም የሚችለው መብት የሚሰጠው የስምምነቱ አንቀጽ በሥራ ላይ እስካለ ድረስ ብቻ ሆኖ ፣ ሦስተኛው አገር አንቀጹ ተፈጻሚ እንዲሆን የመጠየቅ ሕጋዊ መብት ስለሌለው ተስማሚዎቹ አገሮች በማንኛውም ጊዜ ለሦስተኛው አገር መብት የሚሰጠውን አንቀጽ የማሻሻል ወይም የመሠረዝ መብት አላቸው የሚል ነው ።[33]

ሁለተኛው አቋም ዓለም አቀፍ ስምምነቱ በተስማሚዎቹ አገሮች መካከል ተፈጻሚነቱ እስካልተቋረጠ ድረስ የሦስተኛው አገር የተጠቃሚነት መብት እንደተጠበቀ ይቆያል የሚል ነው ። በዚህ አቋም ፣ ሦስተኛው አገር ሳይስማማበት ተስማሚዎቹ አገሮች ለሦስተኛው አገር ስጥተውት የነበረውን መብት በሌላ ስምምነት ማስቀረት እንደሚችሉ ግልጽ ነው ።[34]

---

27 ለምሳሌ ፣ ምንም እንኳን ተስማሚዎቹ ብሔሮች ትልቋ ብሪታንያ ፣ የተባበሩት የአሜሪካ መንግሥታት እና ፓናማ ብቻ የነበሩ ቢሆንም ፣ እ ኤ አ በ፲፱፻፩ ዓ/ም በታላቋ ብሪታንያ እና በተባበሩት የአሜሪካ መንግሥታት የተደረገው የሽይ ፓውንስፎተ ዓለም አቀፍ ስምምነት እና እ ኤ አ በ፲፱፻፫ ዓ/ም በተባበሩት የአሜሪካ መንግሥታት እና በፓናማ መካከል የተደረገው የሽይ ቨሪላ ዓለም አቀፍ ስምምነት የፓናማ ካናል ለማንኛውም አገር የንግድ መርከብና የጦርነት መርከብ ክፍት እንደሚሆን ይደነግጋሉ ።

28 አንቀጽ ፴፮ ፤ ፓራግራፍ ፩ ።

29 ከላይ የተጠቀሰው

30 ፒ. ሲ. አይ. ጄ. ፓብሊከሽንስ (እ ኤ አ ፲፱፻፴፪ ፣ ሲሪይስ ኤ/ቢ ፣ ቁ 46 ፣ ገጽ 147-8

31 ከላይ በግርጌ ማስታወሻ 10 የተጠቀሰውን ይመለከቷል ።

32 "የተባበሩት መንግሥታት አባል ያልሆነ አገር" አለመግባባቱን በሚመለከት ረገድ "በቻርተሩ እንደተደነገገው አለመግባባትን በሰላማዊ መንገድ የማስወገድ ግዴታ አስቀድሞ ከተቀበለ", "የሚመለከተውን ማንኛውንም አለመግባባት ለሴኩሪቲ ካውንሲል ወይም ለጠቅላላው ስብሰባ ማቅረብ ይችላል " በማለት የሚደነግገውን የተባበሩት መንግሥታት አንቀጽ ፴፭(፪) ትን በተጨማሪ ይመለከቷል ።

33 ኤል ኤ ፖደስታ ኮስታ ፣ ማንዋል ደ ደረክ ኢንተርናስዮናል ፑብሊክ ፣ (ሁለተኛ እትም ፣ በኖስ አይረስ እ ኤ አ ፲፱፻፵፯) ፣ ፓራግራፍ 157 ፣ ኤል ኤም ሞሬኖ ኩታና ፣ ደረኮ ኢንተርናስዮናል ፑብሊኮ ፣ (በኖስ አይረስ እ ኤ አ ፲፱፻፶) ፣ ጂ ሳልቨዩን ፣ "ለ ረግል ዠነራል ደላ ፓይ ፣" ረስወይ ደ ኩር (እ ኤ አ ፲፱፻፴፫ ) በልዩም 46 ፣ ገጽ 29-30

34 ለምሳሌ የሐርባርድ ሪሰርች (ምርምር) አንቀጽ ፲፰(ለ) እንደሚከተለው ይደነግጋል ፤ "አንድ ዓለም አቀፍ ስምምነት በስምምነቱ ተካፋይ ላልሆነ አገር ጥቅም የሚሰጥ ከሆነ ፤ አገሩ ስምምነቱ ፀንቶ በሚቆይበት በማንኛውም ጊዜ ጥቅሙን የመጠየቅና የማስፈጸም መብት አለው ።

ሦስተኛው አቋም ፣ ተስማሚዎች አገሮች ከፈቀዱ በሚያደርጉት ስምምነት ለሦስተኛ አገር መብት ለመስጠት ይችላሉ ፤ መብቱ ከተሰጠ በኋላ ማስቀረት የሚቻለው ግን ባለመብቱ ሦስተኛው አገር ሲስማማበት ብቻ ነው[35] የሚል ነው ።

በዚህ ከላይ በተገለጸው ሕግ መሠረት በሌሎች ተስማሚ አገሮች በተደረገ ስምምነት የተገኘ መብት አለ ወይስ የለም የሚለው ጥያቄ እያንዳንዱን ስምምነት በመመርመር የሚመለስ ጥያቄ ሆኖ ፣ ሦስተኛው አገር መብት አለኝ ማለት የሚችለው ተስማሚዎቹ አገሮች በስምምነቱ ግዴታ ለመቀበል ሲፈቅዱ ብቻ ነው ። ቋሚው ዓለም አቀፍ ፍርድ ቤትም በፍሬ ዞንስ ጉዳይ በ፲፱፻፴፪ ዓ/ም በሰጠው ፍርድ[36] የወሰደው አቋም ይኸው ነበር ።

አንዳንድ ጊዜ ይህን ጥያቄ ዓለም አቀፍ ስምምነቱ ራሱም ይወስነዋል ። ለምሳሌ በቨርሳይ ዓለም አቀፍ ስምምነት በአንቀጽ ፫፻፹ እንደተደነገገው ፣ በዚህ ስምምነት በአንቀጽ ፫፻፹[37] የተሰጠው መብት ተፈጻሚ ይሁንልኝ በማለት የፍርድ መፍትሔ መጠየቅ በስምምነቱ ተካፋይ ባይሆንም የማንኛውም አገር መብት ነው ።

እርግጠኛ የሆነ የማይሻር መብት የመስጠት ፈቃድ በግልጽ የሚታይ ወይም ከነገሩ አካባቢ ሁኔታ የሚወሰን ሊሆን ይችላል ─ ለምሳሌ ያህል ፣ በአንድ የሰላም ዓለም አቀፍ ስምምነት አንድ መንግሥት ከግዛቱ ውስጥ በከፊል ለሌላ መንግሥት አሳልፎ ለመስጠት ግዴታ ቢገባም ፣ የሦስተኛው አገር መብት ግልጽ የሆነና የማይሻር መብት ካልሆነ ይህ ስምምነት ግቡን ሊመታ አይችልም ።[38]

በሌላ በኩል የማይሻር መብት የመስጠት ፈቃድ ያልነበረ ለመሆኑ ከዓለም አቀፍ ስምምነት ታሪክ እና ከነገሩ ሁኔታ ማየት ይቻላል ። ለምሳሌ ፣ የአሜሪካ ሴኔት በሔይፓውንስፎተ ዓለም አቀፍ ስምምነት የመጀመሪያ ረቂቅ ውስጥ በፓናማ ካናል በመርከብ መጠቀምን በሚመለከት ረገድ ሦስተኛ አገሮች ስምምነቱን ለማጽደቅና ለመቀበል ስለሚችሉበት ሁኔታ ተደንግገው የነበሩትን አንቀጾች አስቀርቷል ። እነዚህ የስምምነቱ አንቀጾች የተሰረዙት ለሦስተኛ አገሮች መብት የሚሰጡ ግዴታዎችን ለማስቀረት ታቅዶ ስለሆነ ፣ ይህ ሁኔታ ሊሻሻል የሚችለው ተስማሚዎቹ አገሮች በሚያደርጉት ተከታታይ ስምምነት ይመስላል ።

በ፲፱፻፷፮ ረቂቅ ኮሚሽኑ ከአንድ ዓለም አቀፍ ስምምነት ለሦስተኛ አገሮች ስለሚመነጭ መብት ሆነ ግዴታ የወሰደው አቋም መብቱን ሆነ ግዴታውን የሚሰጠው አንቀጽ "የሚሰረዝ መሆኑ ከስምምነቱ ካልተረጋገጠ በቀር ፣ ሊሰረዝ ወይም ሊሻሻል የሚችለው በሦስተኛው አገር ስምምነት ብቻ ነው"[39] የሚል ነው ።

ነገር ግን ስለዚህ ጉዳይ በኋላ በተደረገው ውይይት ከላይ የተጠቀሰው የ፲፱፻፷፮ ረቂቅ ተስማሚዎቹ አገሮች ለሦስተኛ አገር ጥቅም ያደረጉትን ስምምነት የመሰረዝ ወይም የማሻሻል መብታቸውን አለአግባብ ያጠብባቸዋል ፤ ለሦስተኛው አገር የተሰጠው መብትም አላግባብ ነው[40] የሚል አቋም በአንዳንድ መንግሥታት ለኮሚሽኑ ተገለጸ ። ከዚህም ሌላ ተስማሚ አገሮች ለሦስተኛ አገሮች መብት ከመስጠት እንዲቆጠቡ በመገፋፋት የአገሮችን የአሠራር ነፃነት ያደናቅፋል ። እነዚህን ሁኔታዎች በመገንዘብ ኮሚሽኑ በ፲፱፻፷፮ ረቂቅ የሦስተኛ አገር መብት ሊሰረዝ የማይቻለው መብቱ የማይሻር መብት መሆኑ ወይም ያለ ሦስተኛው አገር ፈቃድ የማይሻሻል መሆኑ ሲረጋገጥ ብቻ ነው[41] በሚል ሕግ የ፲፱፻፷፮ ረቂቁን አሻሽሎታል ።

ስለዚህ ለሦስተኛ አገር የተሰጠው መብት የማይሻር መሆን አለመሆኑ መወሰን ያለበት የዓለም አቀፍ ስምምነቱን ይዘት ወይም ተስማሚዎቹ አገሮችና ሦስተኛው አገር ያደረጉትን ስምምነት ወይም መግባባት መሠረት በማድረግ እያንዳንዱን ጉዳይ በመመርመር ነው ።

ነገር ግን ፣ የሦስተኛ አገር መብት ሊሰረዝ ወይም ሊሻሻል የሚችለው መብቱ በተስማሚዎቹ አገሮች ሊሠረዝ ወይም ሊሻሻል እንደሚቻል ታቅዶ የተሰጠ መብት መሆኑ ሲረጋገጥ ብቻ ነው የሚለው ሕግ ግዴታ ለማስቀረት የሦስተኛው አገር ስምምነት አስፈላጊ ነው ከሚለው ጋር ሲነፃፀር ግራ የሚያጋባ ሕግ ነው ።

---

35 ጀ. ኤል. ባየርሊ ፣ "ረግል ጀነራል ዱ ድርዋ ደ ላ ፕይ" ረስወይ ደ ኩር (እ ኤ አ ፲፱፻፴፮) ኤፍ ኤል ፣ አፕንሐይም ፣ ከላይ የተጠቀሰውገጽ 927 ፣ ኤ. ጀ. አረካጋ ፣ ከላይ የተጠቀሰው ፣ ገጽ 344-45

36 ፒ ሲ አይ ጀ ፓብሊከሽንስ (እ ኤ አ ፲፱፻፴፪) ፣ ሲርይስ ኤ/ቢ ፣ ቁጥር 46፣ ገጽ 147-8

37 "የክየል ካናል እና አካባቢዎቹ ለማንኛውም ከጀርመን ጋር በሰላም ለሚገኝ አገር የንግድ ወይም የጦር መርከቦች ፍጹም በሆነ እኩልነት ክፍትና ነፃ ይሆናል ።"

38 ለምሳሌ ኡራጉዋይ ነፃ ሆና የወጣችበት በአርጀንቲናና በብራዚል መካከል እ ኤ አ በኦክቶበር ፳፯ ቀን ፲፰፻፳፰ ዓ/ም የተደረገ የሰላም ስምምነት ።

39 የእ ኤ አ ፲፱፻፷፮ ዓ/ም ረቂቅ ፣ አንቀጽ ፴፪ ።

40 ሪፖርት - ሳፕሊመንት (ማሟያ) ቁ ፱/ኤ6309/ረብ 1 / ቦልዩም 2 ፣ ገጽ 60

41 እንደዚሁም የቪየናው ዓለም አቀፍ ስምምነት አንቀጽ ፴፯ ።

## *መደምደሚያ ።*

የቪየናው ስምምነት (ኮንቬንሽን) በዓለም አቀፍ ወንዞች ወይም ባሕረ ሰላጤዎች የመጠቀም መብትን ፤ ወይም አንዳንድ አካባቢዎችን ወይም ግዛቶችን ገለልተኛ ወይም ከጦር ትጥቅ ነፃ ስለማድረግ እንደተደረጉት ዓለም አቀፍ ስምምነቶች ተጨባጭ የዓለም አቀፍ ሕግን ለመደንገግ[42] የታቀደ ስምምነት አለመሆኑ መገንዘብ ይገባል ። ልማድ (ካስተም) አንዳንድ ጊዜ በአንድ ዓለም አቀፍ ስምምነት የተደነገጉትን ሕግጋት ከተስማሚዎቹ አገሮች ውጭ ተፈጻሚ ዓለም አቀፍ ሕግ እንዲሆኑ የሚያደርገውን አስተዋጽኦ በመገንዘብ ስምምነቱ ያቀፋቸው አንቀጾች "በዓለም አቀፍ ሕግ ተቀባይነት ባገኘው የዓለም አቀፍ ልማድ መሠረት በሦስተኛ ብሔሮች ተፈጻሚ መሆን የሚገባቸውን ሕጎች ተፈጻሚ ከመሆን አያግዱም"[43] በማለት ይደነግጋል ። ምንም እንኳን ይህ አንቀጽ የሚገኘው ዓለም አቀፍ ስምምነቶችና ሦስተኛ አገሮች በሚለው በስምምነቱ ክፍል ከሚገኙት አንቀጾች ውስጥ በመጨረሻ ቢሆንም ለጉዳዩ መሠረታዊ የሆነውን ጥያቄ ይነካል ።

ዓለም አቀፍ ግንኙነትና በአገሮች መካከል የሚደረጉ ግንኙነቶች እየተስፋፉ በመሄድ ላይ መሆናቸውን ስንመለከት ፤ "ፓክታ ኢንፋቮረም ተርቲ" ወይም "ፓክታ ኢን ደትሪመንቱም ተርቲ" የሚባሉት የቆዩ አስተሳሰቦች አግባብ እንደሌላቸው እንገነዘባለን ። የአሁኑ የዓለም አቀፍ ስምምነቶች ሕጋዊ ይዘት እንደዚህ በቀላሉ ሊታይ አይቻልም ። በአሁኑ ዘመን ዓለም አቀፍ ስምምነቶች አብዛኛውን ጊዜ በስምምነቶቹ ባልተሳተፉ አገሮች ላይ መብቶችና ግዴታዎች ይመሠርታሉ ።[44] በሌላ በኩል ሲታይ ሦስተኛዎቹ አገሮች የትኞቹ ናቸው ብሎ ለመወሰን ያስቸግራል ። አንዳንድ ጊዜ በስምምነቱ አባላት ያልሆኑ አገሮች ስምምነቱን ለማዘጋጀት በሚደረገው ስብሰባ ተመልካቾች በመላክ ወይም ተስማሚ አገሮችን በማማከር[45] በስምምነቱ ድርድር ይካፈላሉ ። ምንም እንኳን በቪየናው ዓለም አቀፍ ስምምነት የተቀነባበሩት ሕጎች ጥቅማቸው በቀላሉ የማይገመት ቢሆንም ፤ በአሁኑ ጊዜ እና ለወደፊቱም በጣም አስፈላጊ የሆነውና ትኩረት ሊሰጠው የሚገባው በዘልማድ የሚመሠረቱት ሥነ ምግባሮች በልማዳዊ ዓለም አቀፍ ሕግ ተቀባይነት አግኝተው "ኢዩስኮገንስ" ማለትም የዓለም አቀፍ ጠቅላላ ሕግ አካል ስለሚሆኑበት ሁኔታ ነው ።

---

42 ለምሳሌ የኑረምበርጉ ዓለም አቀፍ ጦር ፍርድ ቤት በመሬት ስለሚደረገው ውጊያ በሔግ ዓለም አቀፍ ስምምነት (ኮንቬንሽን) የተደረጉት ስምምነቶች ተፈጻሚነት ያላቸው ከልማድ የመነጨ የዓለም አቀፍ ሕግ መሆናቸውን ገልጿል ።

43 አንቀጽ ፴፰ ።

44 ለምሳሌ የፖትስዳሙ ዓለም አቀፍ ስምምነት ተሸናፊዋ ጀርመኒ ግዛት እንድትለቅ ግዴታ ሲጥልባት ፤ በዚሁ አኳያ ፖላንድ ግዛት እንድታገኝ መብት ሰጥቷታል ። ጀርመኒ እና ፖላንድ በስምምነቱ አልተካፈሉም ።

45 ለምሳሌ የፖትስዳም ዓለም አቀፍ ስምምነትን በሚመለከት ረገድ ፤ ፖላንድ በዚህ ሁኔታ ትገኝ ነበር ።